## በሲያትል ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ገንዘብ ለማሰባሰብ በተካሄደ ዝግጅት ከ1.15 ሚሊዮን ብር  በላይ ድጋፍ ተገኘ

በሲያትል ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለሕዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ ለማሰባሰብ ያዘጋጁት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት ጥቅምት 5/2004 ተካሂዷል:: በምሽቱ ቁጥራቸው ከ 500 በላይ የሚሆን ከልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጡ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል::

የሶማሌ ፣የትግራይ፣ የኦሮምያ፣ የአማራ ኮሚኒቲ ተወካዮች እንዲሁም የሶማሌና ትግራይ ሴቶች ተወካዮች ባደረጉት ንግግር የታላቁ ሕዳሴ ግድብ አገራችን የጀመረቻቸውን የልማት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ትልቅ ድርሻ ያለው መሆኑን በማስገንዘብ ለግድቡ መጠናቀቅም ሆነ ለእድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ ስኬት የሚያደርጉትን ተሳትፎ አጠናክረው የሚቀጥሉ መሆናቸውን አስታውቀዋል::

የዕለቱ የክብር እንግዳ አምባሳደር ዘሪሁን ረታ በሎስአንጀለስ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቆንሱል ጄኔራል ባደረጉት ንግግር በአገራችን እየታየ ያለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ላስከተለውና በከፍተኛ መጠን እያደገ ያለውን የሀይል ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል የሀይል አቅርቦት እንዲኖር መንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መቅረፁን በእዚህም  የሀይል ማመንጨት አቅማችንን 2000 ሜጋ ዋታ ማድረስ መቻሉን አስረድተዋል:: ግንባታው እየተካሄደ የሚገኘው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ለፈጣን የአገራችን ልማት አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ሀይል ምንጭ በመሆን ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለተያያዝነው ትግል ቁልፍ ድርሻ የሚኖረው መሆኑን አመልክተዋል::

የአገራችን ህዝቦች ለሕዳሴው ግድብ እውን መሆን ከዳር እስከ ዳር በመንቀሳቀስ እየሰጡ ያለት ምላሽ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየ እንደሆነ ገልፀው በአንዳንድ አገሮች ተፅዕኖዎች ምክንያት የዓለም ዓቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ድጋፍ ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው አገራችን እስከዛሬ የተሰሩትን የሀይል ማመንጫ ግድቦችን በራሷ አቅም ለመሸፈን  እንደተገደደችና  የታላቁ የህዳሴ ግድብ ዕጣ ፈንታም ተመሳሳይ በመሆኑ ወጪውን ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ የሚሸፍኑት መሆኑን አስገንዝበዋል:: እየጎረፈ ያለው ህዝባዊ ድጋፍም ለውጭ ተፅዕኖ ላለመንበርከክና በአገራችን ታሪክ ልዩ ስፍራ ለሚይዘው ለእዚህ ግዙፍ ፕሮጀክት እውን መሆን ያለንን ቁርጠኝነት እንደሚያረጋግጥ አስገንዝበዋል:: በውጪ የሚኖረው

ማህበረሰብም አገራችንን በድህነትና በኋላ ቀርነት የሚያሳውቃት የአገራችን ገጽታ እንዲለወጥና ከተመጽዋችነት እንድትላቀቅ በሙሉ ልቡና አቅሙ በድህነት ላይ እየተሄደ ያለውን ትግል መቀላቀል እንዳለበት በማስገንዘብ ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግና ቦንድ በመግዛት እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ በዕለቱም ስለቦንድ ግዢ አፈፃፀም ገለፃ ተደርጓል፡፡

በምሽቱ ከ 67301 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ወይም ከ 1.15 ሚሊዮን ብር በላይ ከቦንድ ሽያጭና ስጦታ ተገኘ ሲሆን ከ26,750 ዶላር ወይም ከ455,270 ሺ. ብር በላይ ደግሞ ቦንድ ለመግዛትና ስጦታ ለማድረግ ቃል ተገብቷል፡፡